# የታረመ ምላስ

እኔ ፤ እኔ ብቻ ፤ ሲሆን ፤ ድሩም ማገ
ባለጊዜ ስናይ ፤ ማርገድ ማደግደገ
ገንዘቡ ሲያጓጓን ፤ ስምና ማዕረገ
ድንቁርና ሲነግስ ፤ ተብትቦን ሃረገ
ከዕውቀት የተጣላን ፤ ነንና መፃገ
አይወጣም ካፋችን ፤ መልካምና ደገ ።

ማንም ያልነበረ ፤ ምንም ያልነበረ
የደንቆሮ አበጋዝ ፤ ጭፍን ያልተማረ
ገንዘብ አለኝ ብሎ ፤ ከተወጣጠረ
ያከበረውን ሕዝብ ፤ ንቆ ከደፈረ
ከወገኑ ገዳይ ፤ ከጠላት ካበረ
　　በሩጫ እንደመቅደም ፤ መስሎይ የሰመረ
　　አፉንም እንደግሩ ፤ ማስሮጥ ከጀመረ
　　ትግላችን ካልገባው ፤ ከተንሸዋረረ
　　እሱም ይደቆሳል ፤ ሆኖ እንዳልነበረ
　　ሕዝብን መዳፈሩ ፤ ማሞጥሞጥ ካልቀረ ።

ዝምታም ፤ ወርቅ ነው ፤ መታገል ባይሹ
እስራት ግርፋት ፤ ሞትንም ቢሸሹ
የተለመደ ነው ፤ በትልቅ ትንሹ
ግና ያለቦታው ፤ ሰዎች ሲያቀረሹ
አያገባ ገብቶ ፤ ነገር ሲያበላሹ
የከፋ ይሆናል ፤ አፀፋ ምላሹ ።

ካንድ ቤት ፤ ሶስት አራት ፤ እየተገደለ
ግፍና መከራው ፤ ሞልቶ ፤ ፈሶ እያለ
የተጨቆነው ህዝብ ፤ መሮት በታገለ
ባልተሟሸ ምላስ ፤ ባልተስተካከለ
አፍ እንደ ማራቶን ፤ ቀደም ቀደም ካለ
ሊገራ ግድ ይላል ፤ ድንበር ከዘለለ ።

ቢሆን ሸጋ ነበር ፤ እየተስተዋለ
ኑሮህ የተመቸ ፤ የሚነካህ የለ
ፖለቲካ እሩጫም ፤ አሎምፒክ አይደለ
ስርአት ቢለወጥ ፤ ፋሽስትም እስካለ
ሰውን ሳይነካኩ ፤ ሊኖር እስከቻለ
በሌሎች ሰቆቃ ፤ ባትቀልድ ምናለ
ባታዝንለት እንኳን ፤ ዝምታም እኮ አለ
የታረመ ምላስ ፤ መቼ ሰው ገደለ ።

ታዛቢው
March 16, 2018